# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 27

ነሐሴ 15 ቀን 2014ዓም(21-08-2022)

በዛሬው ዓምዳችን ነገራት ካለመለወጣቸው የተነሳ ብዙም የምንለው የተለዬ ባይኖርም ካለፈው ሳምንት ቅጥያ ሆነው ከዘለቁት ዋና ዋና ጉዳዮች በመነሳት የሰሞኑን ገጠመኞች ገረፍ ገረፍ የምናደርግበት ይሆናል።በሰሜኑ ያገራችን ክፍል በጦርነት አውድ ጥላ ስር መሆኑ ይበልጥ ጨመረ እንጂ አልቀነሰም፣ወያኔ ለመውረር የጦርነት ነጋሪት ከመጎሰም አልፎ ብዙ ሃይል አሰልፏል። የወልቃይትንና የራያን መሬት የማይደራደርባቸው እንደሆኑ በመግለጽ በድርድርም በጉልበትም እወስዳለሁ ብሎ ተነስቷል።የአብይ አህመድ መንግሥትም ከአማራው ነጥቆ ለመስጠት በሕገመንግሥቱ መሠረት ይፈታል የሚል የውሰዱ ፈቃዱን በተዘዋዋሪ ይናገራል።ለአብይ አህመድ ሥልጣኑ እስካልተነካ ድረስ ከሰማይ በታች ባሉት ሁሉ ለመደራደር ቦታና ቀን እንደማይመርጥ ይፋ አድርጓል።የወያኔን ድፍረትም ሆነ የኦሮሙማውን የማዳከምና የከበባ ሴራ መቋቋምና ማምከን የሚቻለው ጉዳዩ የሚመለከተው ማህበረሰብ በተለይም አማራው በቅጡ ተደራጅቶ በአንድ ዓላማና በአንድ ግንባር ተሰልፎ በመታገል የራሱንና የአገሩን ፣የኢትዮጵያ ህልውና ማስመለስ በሚችልበት ቁመና ላይ መገኘት አለበት እንላለን።የጀመረው መነሳሳት እንደተጠበቀ ሆኖ የፋኖ አደረጃጀት ከተግባር ጋር የተያያዘ መሆን አለበት እንላለን።መሣሪያ ተሸክሞ በከተማ ማውደልደልና በአነግ ባንዲራ ላይ ያለውን የጣኦት ዛፍ የመሰለ ጎፈሬ ነስንሶ መታዬት ብቻ ሳይሆን መሣሪያውንም ከጥቅም ላይ በማዋል ትርጉም ያለው ተጋድሎ ማድረግ ይጠበቅበታል።ሊበላው ያሰፈሰፈው ጅብ በጩኸት ብቻ እንደማይምረው ሊያውቀው ይገባል።ጫካ መግባት ማለት እርምጃ ወስዶ የሚያፈገፍጉበት፣ዳግም ለማጥቃትም የሚዘጋጁበት የአርበኞች ክልል እንጂ ሸሽቶ ድምጽ አጥፍቶ የሚደበቁበት ውድማ ማለት አይደለም። የኦሮሙማው ብልጽግና መንግሥት ከእጀታው ከብአዴን ጋር በመተባበር ፋኖን ለማጥፋት በተደጋጋሚ ሙከራ አድርጓል።ለሙከራው ግን ተመጣጣኝ መልስ አልተሰጠውም።በአቅም ማነስ ከሆነ አቅሙ የሚጎለብትበትን መንገድ ሁሉም አማራ፣እንዲሁም ለኢትዮጵያ አንድነት ቆሜያለሁ የሚል ዜጋ ሁሉ መተባበር አለበት።በገንዘብ፣በስንቅና ትጥቅ ብሎም በሰው ሃይል ሊሳተፍ ይገባል።

ባለፈው ዝግጅታችን የአማራ ተወላጆች አዲስ አበባ እንዳይገቡ መከልከላቸውን መግለጻችን ይታወሳል።ችግሩ በከፊል ተቃለለ የሚል ወሬ ሾልኮ የወጣ ቢሆንም አሁንም አትገቡም ተብለው በስቃይ ላይ የሚገኙ ወገኖች እንዳሉ ለማወቅ ችለናል።ይህ ለምን እንደሚደረግ ባለፈው የገለጽነው ሲሆን የአዲስ አበባን የሕዝብ ስብጥር (Demography)ለመለወጥና አዲስ አበባን ለመሰልቀጥ ካለ ዓላማ እንደሆነ እኛ ብቻ ሳንሆን ሌሎቹም የሚመሰክሩት ሃቅ ነው።በተግባርም የተረኛውን የኦሮሙማ ቁጥር በማብዛት ረገድ ብዙ ሥራዎች መሠራታቸውን ታዝበናል።ቤቱም፣ሥራውም፣ትምህርቱም ንግዱም---ወዘተ የሚታደለው ለዚሁ በተረኝነት የእውር እብድ ለሆነው ቡድን ተወላጅ መሆኑ አገር ያወቀው ጸሐይ የሞቀው ሃቅ ነው።ልደብቅህ ቢሉት የማይደበቅ ተራራ ያህል ግዝፈት ያለው የወገንተኝነት ሥራ ነው።መሪዎቹም ቢሆኑ በኩራትና በድፍረት ያመኑት ጉዳይ ነው።ሆኖም ግን መታወቅ ያለበት ሁሉም የኦሮሞ ተወላጅ ተጠቃሚ አይደለም።ብዙሃኑ በዛው የጭርንቁስ ኑሮ ውስጥ እንደሌላው ወገኑ፣እንደአማራው፣ትግሬው፣ወላይታው፣ሶማሌው፣አፋሩ፣ሲዳማው---ወዘተ የሚኖር ነው።የሁሉም ጎሳ ተወላጅ በስሙ ሥልጣኑን ይዘው ከፋፍለው በሚገዙት የሚረገጥና የሚበዘበዝ እንጂ አንዱ ከሌላው በተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ አይኖርም።ከዬጎሳው የተውጣጡ ጥቂት አድርባዮችና አጫፋሪዎች ብቻ የዘረፋው እንጥፍጣፊ ተቋዳሾች ናቸው።

በግንባር ቀደም የስቃዩ ሁሉ ሰለባ የሆነው የአማራ ተወላጅ እንደሆነ ሁሉም ያውቀዋል።አዲስ አበባ ከተማ እንዳይገባ የመታገዱ ዜና ምንም እንኳን በስፋት የሚነገር ቢሆንም በአውቶብስ ብቻም ሳይሆን በአውሮፕላን በቦሌ በኩል በሚገቡትም ላይ ተመሳሳይ የማጉላላትና የማንጓጠጥ ፣አልፎ ተርፎም ከዬት መጣህ?ለምን መጣህ፣አድራሻህ የት ነው በሚሉ ጥያቄዎች በጉዞ የደከመን ዜጋ እንደ ውጭ አገር ቱሪስት በጥያቄ የማፋጠጡ ተግባር እንደሚካሄድ ለማወቅ ችለናል።ይህም አንዱ የከተማዋ ባለቤት አይደለህም የሚለውን መልእክት በሾርኒ ማስተላለፍ ሲሆን የደህንነቱንና የኢሚግሬሽኑን ቦታ የሚቆጣጠረው እብሪትና ዕብደት የወጠረው ኦሮሙማው ተረኛ በመሆኑ አይደረግም አንልም። እንኳንስ አዲስ አበባን ቀርቶ ወሎን፣ቤንሻንጉልን፣ጎጃምን አልፎ ተርፎ ወልቃይትንና ሁመራን ለመዋጥ የቋመጠ ጅብ አይሉት ጅል የሚያካሂደው ተግባር ከሆነ ውሎ አድሯል።የቅርቦቹንማ በታትኖ ለመዋጥ የሚያደርገው ሴራ በደቡብ ያገራችን ክፍል በገሃድ እዬታዬ ነው።

ከአንድ ወር ወዲህ እዬተካረረ የመጣው ክልል የመሆን ጥያቄ በጉራጌው ማህበረሰብና በወላይታው እንዲሁም በሌሎቹ በኩል የሚሰጠው ምላሽ በመጠበቅ ላይ መሆኑ የሚታወቅ ነው።በፌዴራል ተብዬው ውሳኔ ይሰጥበታል የተባለው ይህ የሕዝብ ጥያቄ ተድበስብሶ ለተወሰኑት የክላስተር ይበሉት የፕላስተር የመሆን ምላሽ ሲሰጠው የጉራጌና የወላይታ ማህበረሰብ ግን ለጠዬቀው ክልል የመሆን ጥያቄ አይሆንም የሚል መልስ ተሰጥቶታል።እምቢ መባልም ብቻ ሳይሆን እንደ ጠላት በመከላከያ ጦር ተከቦ ለተቃውሞ እንዳይወጣ ታፍኗል።አስተባባሪ ናቸው የሚባሉትም እዬተለቀሙ ወደ አልታወቀ እስርቤት ተወርውረዋል።

የጉራጌና የወላይታ ማህበረሰብ ጥያቄ የዴሞክራሲ ጥያቄ ስለሆነ መልስ ማግኘት አለበት የሚል አቋማችንን አሁንም እንደግማለን።ምንም እንኳን በክልል መካለሉን የምንቃወመው ቢሆንም፣ለጉራጌና ለወላይታ ማህበረሰብ የሚነፈግ ለሌላው የሚሠጥ መብት እንዳልሆነ እናምናለን።የኦሮሙማው ተረኛ ቡድን የነዚህን ማህበረሰቦች ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ያልፈለገው ክልል ከሆኑ በመዳፋችን ውስጥ አስገብተን ልንጨፈልቃቸውና ልንቆጣጠራቸው አንችልም፤ከአማራውና ከኢትዮጵያዊነት ጋር ካላቸው ታሪካዊ ትስስርና የኢትዮጵያዊነት ጠንካራ አቋም የተነሳ ምኞታችንን ልናሳካ አንችልም ከሚል ስጋት የመነጨ እንደሆነ አይካድም።

የጉራጌና የወላይታ ማህበረሰብ በዚህ መለስተኛ ጥያቄው የሚያስፈራ ከሆነ ከአማራው ጋር የነበረውን ታሪካዊ ግንኙነቱን ሳይበረዝ አጠናክሮ ትልቁን የኢትዮጵያዊነትን ዓላማ አንግቦ ከቀጠለበት ይበልጥ ያስፈራል።ማስፈራትም ብቻ ሳይሆን የኦሮሙማው አገር አጥፊ ቡድንና ያሰፈነው የጎሰኞች ሥርዓተ ግባተ- መሬቱ የቅርብ ጊዜ ይሆናል የሚል እምነት አለን።የኦሮሙማው ቡድን ስጋትም ይኸው ነው። ስለሆነም ለሁለቱም ማህበረሰብ ተወላጆች ትግላቸውን አጠናክረው መቀጠል አለባቸው እንላለን። የነብር ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁምና!

ያሰብከው ባይሞላ ሁኔታው ቢጠጥር፣

ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር!!

የጉራጌና የወላይታ ሕዝብ ሆይ!በትግልህ ውስጥ ክፍተትና ድክመት ካለበት አስተካክለህ፣ከራስህ የአካባቢ ጥያቄ ወጥተህ እንደ አንተው ለመብቱና ለአገሩ አንድነት ከሚታገለውና መስዋእት ከሚከፍለው ከአማራው ወገንህ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘህ ታግለህ የአገርህና የመብትህ ባለቤት ሁን! መብት በትግል እንጂ በልመናና በደጅ ጥናት አይገኝም።

ሌላው አንገብጋቢ እርዕስ በባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ ዙሪያ የተከሰተውና ያልተቋጨው ውዝግብ ነው።በፓርቲው ውስጥ የተከሰተውን በሚመለከት ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዝግጅቶቻችን ላይ ከማስረጃ ጭምር ማቅረባችን ይታወሳል።አሁንም ድረስ ይህ ነው የሚባል ግልጽና የሚታመን ማብራሪያ አልተሰጠም።ፓርቲው በውዝግብ በመናጥ ላይ ነው። የሥራ አመራሩን ቦታ የያዘው ቡድን ለጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ ስለአቶ እስክንድር  የት እንዳለ አላውቅም እያለ አያይዞ ደህና ነው የሚል ምላሽ ሲሰጥ ተሰምቷል።ለመሆኑ ዬት እንዳለ የማይታወቅ ሰው ደህንንቱን በምን ሊያረጋግጡ ይችላሉ?ብቻ መሪያችን መሪያችን ከማለት ያለፈ ስለመሪው ሁኔታ አለማወቁን ባይታመንም ለማሳዬት ሞክሯል።እስክንድር አረገ? ወይስ የመሰወር ምትሃት አለው?ወይስ ታፈነ?የእኛም ጥያቄ ነው። እባብ ለባብ ይተያያል ካብ ለካብ በሚመስል መልኩ ቀደም ሲል የፓርቲው አመራር አባል የሆነችው ወ/ሮ አስካለ ደምሌ ከሰጠችው ጋር የሚቃረንና እንደውም የወይዘሮ አስካለ ስምና ያወጣችው መረጃ በሌሎች የሚድያ ዘርፎች አለመወሳቱ የሴራውን ስፋትና ጥልቀት የሚያሳይ ይመስለናል።ሴራውም ከኢትዮጵያ እስከአሜሪካ በተዘረጋ ሰንሰለት የተሳሰረ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አድሮብናል። ግምትም ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል የድርጅቱ የውጭ ግንኙነት ሃላፊ የነበረው አቶ ገለታው ዘለቀ ከድርጅቱ መውጣቱ በሚስጥር የተያዘ ሲሆን ያለምክንያት የሆነ ነው ለማለት አንደፍርም። ከቀናት በፊት የአውሮፓው የድጋፍ ኮሚቴ ባወጣው መግለጫ የአሜሪካው የድጋፍ ኮሚቴና በአገር ቤት ያለው የአሁኑ  የፓርቲው አመራር አባላት በጥምረት ያደረጉት ሴራ ነው ሲል በግልጽ ይፋ አድርጓል።አሁን ያለውንም አመራር በቀጥታ ስርዓተ አልባና ጸረ ባልደራስ ነው ሲል ከሶታል።ይኸው ልዩነት ከተካረረ የፓርቲው ህልውና መዳከም ብቻ ሳይሆን የመቀጠሉም ነገር አጠያያቂ ነው።የፓርቲውን መፈራረስ የሚሹ ከአብይ አህመድ ጀምሮ ሌሎቹ የግንቦት ሰባትና መሰሎቻቸው ካላቸው የሥልጣን ቦታና ጉልበት ጋር ሲደመር ከተቻለ የነሱ ፈረስ የሚጋልብበት አለያም በምርጫ ቦርድ በኩል እውቅናውን እንዲገፈፍ ከማድረግ አይመለሱም።

ከአንዳንድ የዩትዩብ አናፋሾች በኩል እንደሚሰማው ከሆነ አቶ እስክንድር በአሜሪካ ቆይታው ከ600 ሽህ ዶላር በላይ መሰብሰቡና ያንንም ገንዘብ እንዳላስረከበ ተደርጎ ይወራል።ከተደጋጋሚ የአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች ውድቀት ታሪክ ስንነሳ ገንዘብና ሥልጣን ለመከፋፈልና ለመፍረስ ዋና ምክንያቶች እንደሆኑ አይካድም።ይህ ሁኔታ ግን በባልደራስ ውስጥ በተለይም በአቶ እስክንድር በኩል ይፈጸማል ብለን ባናምንም ሆኖም ግን ገንዘቡን ሊቀራመቱ ካሰፈሰፉ ጅቦች መንጋጋ ለማዳን የተደረገ እርምጃ ሊሆን ይችላል የሚለው ሁለተኛው ግምታችን ነው።የቄሳርን ለቄሳር ብለን የባልደራስን ለባልደራስ ከመተው ሌላ አማራጭ የለንም።የሚያሳዝነው ግን አዲስ አበባ በዚህ ቁልቁለት እዬነጎደች ባለችበት ወቅት ሊያድናት የተነሳው ፓርቲ እራሱ የቀውስ ሰለባ ሆኖ መገኘቱ ነው።የፓርቲውን ትርምስ ተከትሎ የአዲስ አበባ አስተዳደር የወሰደው የከተማዋን ቦታዎች የመንጠቅ ሂደት ለፓርቲው መተራመስ የነ አብይና የአዳነች አቤቤ እጅ ያለበት ለመሆኑ ማስረጃ ነው።ባለቤት አልባ ከተማ አድርጎ ያሻቸውን ማድረግ!

 ከተማዋን የመዋጡ ሂደት ባለፉት ቀናት ተጀምሯል።የከተማዋን የቅርብ መንደሮችና ክፍለ-ከተማዎችን በኦሮሙማው ክልል እየጠቀጠቁ አዲስ አበባን የማመንመኑ ሥራው በከፊል ተፈጽሟል።የቀረው ቢኖር ከተማዋን ሙሉ ለሙሉ ነጥቆ በፊንፊኔ ስም በኦሕዴድ ፓስተር ማጥመቁ ነው።አንዷ የከተማዋ ነዋሪ እንዳሉት ተኝቼ  ጧት ስነሳ ቤቴ ሳይነቃነቅ የኦሮሞ ክልል ነዋሪ ነሽ መባሌን ፣ስተኛ የነበረው የኢሕአዴግ ባንዲራ ተነስቶ የኦነግ ባንዲራ ሲውለበለብ አዬሁ ብለዋል።እንዲህ ነው የነአቶ እንደልቡ የእብሪት ሥራ! ነዋሪው ሳያውቀውና ሳይመክርበት እንደ ገበጣ ጠጠር በፈለጉበት ጉድጓድ ውስጥ መጨመር የእውቀትም የታሪክም ድህነት የሚያመጣው ድንቁርና የወለደው እብሪት  ነው።ይህ ሁሉ

ሲሆነ ግን የአዲስ አበባ ሕዝብ በዝምታ ድባብ ውስጥ ሆኖ ከመታዘብ ሌላ የወሰደው እርምጃና ያሰማው ተቃውሞ የለም።

ይህ ድፍረትና ማን አለብኝነት የበለጠ ችግር ይወልድ እንደሁ እንጂ ሰላምና የተሻለ ሁኔታ አያመጣም። ሥራው አዲስ አበባ መኖሪያው ከአዲስ አበባ ውጭ በኦሮሙማ ክልል የሆነ ሰው የሥራና የመኖሪያ ግብር ለማንና ዬት እንደሚከፍል፣በሥራው ላይ ችግር ቢገጥመው ለማን አቤት እንደሚል ሲያስቡት የነበረው ውልግድግድ ችግር በእጥፉ መከሰቱን ለማስተዋል አያዳግትም።በልህና በጥላቻ ብሎም በስግብግብነት የሚነዳ ቡድን አርቆ የማዬትና የማሰብ ችሎታ ይኖረዋል ብሎ ማሰብ በራሱ ድክመት ነው።ሲጀመርም ለነዋሪው ሕዝብ ሳይሆን ለራሳቸው ጥቅም የሚያደርጉት የግብር ይውጣ ሥራ ነው። ሲጀመርም ከወመኔ ጎሰኛ ቡድን መልካም አስተዳደር አይጠበቅም!

የኦሮሙማው አገር አጥፊ ቡድን ያልተረዳውና ያላወቀው ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሱናሚና እሳተገሞራ(ቮልኬኖ) ድምጹን አጥፍቶ ውስጥ ውስጡን እዬተብላላ ሃይሉን አሰባስቦ ሲነሳ የሚያቆመው ምድራዊ ሃይል እንደማይኖር ነው።ለጊዜው ዝም ቢል ፈርቶና ተቀብሎ ሳይሆን ብስጭቱ እንደጥንስስ ውስጥ ውስጡን እዬፈላ ሄዶ ለመገንፈል ጊዜውን በመጠበቅ ላይ መሆኑን ሊያውቁት ይገባል።ማንም ቢሆን ተረግጦና ተዋርዶ ለመኖር የሚሻና የሚመርጥ የለም፣የጊዜ ጉዳይ ነው ሁሉም ነገር እንዳልነበር ይሆናል።ባለፉት 50 ዓመቶች ወዲህ የነበሩት ስርዓቶች መጨረሻቸው ምን እንደሆነ የሚታወቅ ነው።ሁሉም የታሪክ አመድ ሆነዋል ።የአሁኖቹም እንዲሁ የታሪክ አመድ ይሆናሉ።ያውም ለልጆቻቸውና ለልጅ-ልጆቻቸው በሚያሳፍር መልኩ! በሚያሳፍር ኋላቀር የፖለቲካ እምነት የተነሳ!

የዳግማዊ ምንሊክና የባለቤታቸው የእቴጌ ጣይቱ ብጡል እለተ-ልደት በነሓሴ 12 ቀን በተወለዱበት አካባቢ ፣በሸዋና በአንዳንድ ቦታዎች ተከብሮ ውሏል።አጼ ሚኒሊክ (የክርስትና ስማቸው ሳህለማርያም)በፈረንጆች አቆጣጠር በኦገስት 17 ቀን 1844 ተወልደው በ69 ዓመታቸው ባደረባቸው ህመም በዲሴምበር 12 በ1913 ከዚህ ዓለም የተለዩ ሲሆን ባለቤታቸውም እቴጌ ጣይቱ ብጡል( የክርስትና ስማቸው ወለተሚካኤል) ከሰባት ዓመት በኋላ በ1851 ተወልደው በ67 ዓመታቸው በ11 ፌብሩዋሪ 1918ከባላቸው እረፍት ከአምስት ዓመት በኋላ ያረፉ ባለትልቅ ታሪክና ውለታ ንግሥት ናቸው። ነፍሳቸውን ይማርልን እንላለን።መልካም ታሪክ የሠራ ምን ጊዜም ቢሆን በትውልድ ሲመሰገንና ሲወሳ ይኖራል።በአንጻሩምለዚያ ያልታደለው፣ ክፉ የሠራና መናጢ መሪ እንዲሁ በታሪክና በትውልድ ሲረገም ይኖራል። ኢትዮጵያ አገራችንም እነዚህን ሁለቱን ባህሪያት ዬተላበሱ መሪዎች ኖረው ያለፉባት አገር ነች፤ አሁንም ከመናጢዎቹ አንዱ የሆነውን ተሸክማ ወደ ቀጣዩ ለመሻገር እያኮበኮበች ነው።ማረፊያዋ ያማረ፣የሚመጣውም መሪና መንግሥት ፈሪሃ እግዚአብሔርና ፈሪሃ ሕዝብ ያደረበት አንዲሆንላት እንመኛለን ብቻም ሳይሆን ለዚያ ውጤት እንታገላለን።

ከሰሞኑ አወዛጋቢ ክስተቶች አንዱ የሆነው የተባበሩት መንግሥታት የምግብ ተራድኦ ድርጅት ከኡክሬን ገዝቶ ለኢትዮጵያ ያበረከተው የስንዴ እርዳታ ነው።የመንግሥታቱ ድርጅት በኢትዮጵያና በሌሎቹ የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ድርቅ ያስከተለውን እርሃብ 22 ሚሊዮን ሕዝብ መኖሩንና ከዚያም ውስጥ 11 ሚሊዮኑ በኢትዮጵያ ውስጥ መኖራቸውን ባቀረበው ሰንጠረዥ አመልክቷል።እርሃቡን ለመታደግ በማለት ከሁለት ሚሊዮን ሜትሪክ በላይ ስንዴ በመርከብ ጭኖ መንቀሳቀሱን ይፋ አድርጓል።ይህንን ተከትሎ አብይ አህመድ ኢትዮጵያ የገዛችው ስንዴ የለም፣እራሷን ችላ የመመገብ አቅም ላይ መድረሷን ለማጣጣልና ፤የእኛን የስንዴ አምርቶ የመላክ እቅማችንን ለማኮላሸት ሆን ተብሎ የታቀደ የጠላት ሴራ ነው ሲል አጣጥሎታል።እርግጥ ነው ኢትዮጵያ አልገዛችም፤ለመግዛትም አቅሙ የላትም።ያላት የውጭ ምንዛሪ የተመናመነና ግፋ ቢል ለአንድ ወር የሚበቃ ነው ሲሉ የገንዘብና የኤኮኖሚ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።ስለሆነም ባትገዛም አቅም ያላቸው ገዝተውላታል።ይህ ማለትም በስሟ ተገዝቶላታል ማለት

ነው።በመሬት ላይ ያለው ሃቅ ግን ኢትዮጵያ እራሷን ለመመገብ ከምትችልበት ደረጃ ላይ ገና አልደረሰችም።የቦረና ፤የአፋር፣የትግራይ፣የወለጋ---ወዘተ ቁጥሩ ከ11 ሚሊዮን በላይ የሆነ ሕዝብ በድርቅና ሰው ሰራሽ ችግር(በጦርነትና በመፈናቀል ምክንያት ) ለርሃብ እንደተጋለጠና ከብቶቹ ሳይቀሩ እንዳለቁበት የሚካድ አይደለም።ምንም እንኳን ምዕራባውያን እህልን እንደ አንዱ የጦር መሳሪያ አድርገው መጠቀማቸውን የምናውቀው ቢሆንም በዚህ ምክንያት በአገራችን የተከሰተውን የአፄር ለውጥና ሥርዓት ወለድ እርሃብ የለም ብሎ ለመካድ ህሊናችን አይፈቅድም።እርሃብ አለ፣እርሃብን ግን ለማሶገድ የሥርዓት ለውጥ አንዱና ዋናው መፍትሔ መሆኑን እናምናለን።የምዕራባውያን እርዳታም ሆነ ብድር ከነሱ ጥቅምና ፍላጎት ጋር የተሳሰረ መሆኑን ማንም አይዘነጋውም።ዘላቂ መፍትሔም አይሆንም። ቀደም ሲል እምቢ ያሉትን እርዳታ አሁን ላይ እሺ ብለው ሲመጡ ስናይ ምናልባትም በአብይ አህመድና በነሱ መካከል የተደረገ የሚስጥር ስምምነት እንዳለ ለመጠርጠር በቂ መነሻ ነው። የሚፈልጉትን ካላገኙ እንደማይሰጡ ታሪካቸው ይመሰክራል።የዬመንና የአፍጋኒስታን ሕጻናት፣የሶሪያና የፍልስጤማውያን የመከራ ኑሮ ለዚያ በቂ ማስረጃ ነው።በአንድ እጃቸው ጭብጥ ሲሰጡ በሌላው እጃቸው አፍሰው የሚወስዱት መኖሩን ለማወቅ ከያገራቱ የሚሰማውን አቤቱታ ማዳመጡ በቂ ነው። የቀድሞው የፈረንሳይ ፕሬዚደንት የነበሩት ዣክ ሽራክ በመጨረሻው የዕድሜያቸው መገባደጃ ዋዜማ ላይ ያመኑትና የተናገሩት የምስክርነት ቃል የዚያ ማሳያ ነው።በቀውስ የሚከብሩትን ያህል በሰላም ሊያገኙት አይችሉም፤ምክንያቱም በሰላም የሚኖር ሕዝብ ለአገሩ ጥቅምና ክብር ሙሉ ጉልበቱንና እውቀቱን ስለሚያፈስበት ነው።የተዳከመና የተበታተነ፣በችግር የሚማቅቅ ሕዝብ ግን ለቁጥጥርና ለዘረፋ ይመቻል፤በቁራሽ ዳቦ ይደለላል፤ይገዛልም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደምዕራባውያን በስንዴ ፍጆታ የሚታወቅ አይደለም፣ስንዴና አጃ ቢያመርትም እንደመደበኛ ምግብ ከሚወስደው የማይወስደው ይበዛል።የአሁኑን ሳይሆን የነበረውን ስናነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዋናነት መደበኛ ምግቡ፣እንጀራ ሲሆን ለዚያም አገር በቀሉ ጤፍ ከዚያም ገብስ፣ ማሽላ፣በቀሎ፣ዘንጋዳ፣ ለማባያም ምሥር፣አተር፣ባቄላ፣ሽንብራ ጓያና አደንጓሬ የመሳሰሉት ናቸው። የእንሰቱን ብናነሳም፣ጎመን፣ሰላጣ፣ካሮት፣ኮባ(ለቆጮ)፣ቲማቲም፣ከፍራፍሬም ሙዝ፣ሎሚ፣ብርቱካን፣ ትርንጎ በስፋት የለመዳቸውና የሚያመርታቸው ነበሩ። በነበር ቀረ እንጂ!

የበግና የከብት ሥጋም አቅራቢ አገር ነበረች አሁንም ነች።ለመካከለኛው ምስራቅ የአረብ አገሮች በተለይም ለሳውዲ የልኳንዳ ቤት ነች።ገቢው ግን ለሻጮቹና ላሻሻጮቹ እንጂ ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም አልዋለም።ብዙ ነገር ይወጣል፣ይሸጣል!ሕዝቡ ግን በድህነት በርሃብ አለንጋ ይቀጣል።

ከሁለት ቀን በፊት በብዙሃን መገናኛ ስርጭት በኩል የወጣው ዜና የአብይ አህመድ መንግሥት በአገርና በሕዝብ ገንዘብ ተገንብተው አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩትንና ለመስጠት በዝግጅት ላይ ያሉትን ስምንት ትልቅና መለስተኛ የሱካር ፋብሪካዎችን ከመንግሥት እጅ አውጥቶ ለውጭና ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ለመሸጥ ያሳለፈው ውሳኔ ነው።ይህ እርምጃ ለተሻለ ሥራና እድገት ታስቦ ሳይሆን ሻሽጦ ገንዘብ ለመሰብሰብ ካለው የኦሮሙማው ቡድን ፍላጎት የተነሳ ነው ብለን እናምናለን፣ይሸጥ ቢባል እንኳን ቅድሚያ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች መሆን እንዳለበት ብናምንም ግን በዚያም በኩል ቢሆን የሚሸጠው ለኦሮሙማው የጥቅም ተካፋዮችና የጎሳ አባላት ሊሆን እንደሚችል ያለፉት ሽያጮች ሂደት አሳይቶናል። ገንዘብ የሌላቸው ከኦሮሚያ ባንክ እንዲበደሩ ይመቻችላቸዋል፣በግለሰቦቹ ስም ተገዛ ተባለ እንጂ ባለቤቱ ኦሕዴድና የኦሕዴድ አመራር አባላት ናቸው።

የምዕራባውያን አንዱ ጥያቄያቸው(Privatization or stractural adjustment ) በሚሉት ፈሊጦች የመንግሥት ይዞታና ንብረት የሆኑት እንዲሸጡና በግለሰብ እጅ እንዲወድቁ በዚያም ገንዘብና አቅም ያላቸው እነሱ እንደሆኑ ስለሚያውቁ የአገሪቱን የኤኮኖሚ ምንጮች ለመቆጣጠር እንዲያመቻቸው

ሲወተውቱ የኖሩበት ጥያቄ ነው።ቀደም ሲል የኢትዮ ቴሌ በውጭ አገር ዜጎች የበላይ ድርሻ ይዞታችንን አጥተናል።የአሁኑም የስኳር ፋብሪካዎች የጨረታ ውሳኔ የዚያው ተከታይ ነው።የባቡሩም፣የሃይል ማመንጫውም፣የባንኩም ---ወዘተ የሃብት ዝውውርና ቅርምት ለዘላቂው የአሮሙማው አገረ ምሥረታ ዕቅድ የሚረዳ ዝግጅት አካል ነው።ኢትዮጵያን አራቁቶ በማፈራረስ፣ሃብቷንም ተቀራምቶ መፈርጠጥ! ነገ ደግሞ እንደ አንድ ዓይን የሚታዩው የኢትዮጵያ አዬር መንገድ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ሲታሰብ ከዚሁ ከመቀራመትና ከመሸጥ ከመለወጥ ያመልጣል ብለን አንገምትም።የሚነፍሰው ንፋስም ያንኑ የሚያመላክት ነው።የሁለቱ አብራሪዎች በእንቅልፋምነት ከሥራቸው መወገዱ የዚያ መንደርደሪያ ይሆን?የምናዬው ይሆናል።

ነገሩ እንዲህ ነው አንድ የኢትዮጵያ አዬር መንገድ አውሮፕላን ከካርቱም ከተማ ተሳፋሪዎች ጭኖ አዲስ አበባ ቦሌ አዬር ማረፊያ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው ሁለቱም አብራሪዎች ቅልጥ ባለ እንቅልፍ ላይ ወድቀው ከታወር ግንኙነት ጋር በመቋረጣቸው ስጋት ተነስቶ  ባለበት ሁኔታ የአውሮፕላኑ የአደጋ ምልክት ሰጭ ድረሱልኝ ብሎ በመጮሁ ሁለቱም አብራሪዎች ከእንቅልፋቸው ነቅተው በሰላም እንዳረፉ  ተገልጿል።ሆኖም ግን በአዬር መንገዱ ባለሥልጣናት ሁለቱም አብራሪዎች ከሥራቸው ታግደው ሁኔታው በመጣራት ላይ እንዳለ ሰምተናል።እንኳንስ አደጋ ሳይከሰት ተሳፋሪዎቹ በደህና ገቡልን እያልን ጉዳዩ ግን ምናልባት አብራሪዎቹን ለእንቅልፍና ለአደጋ የሚዳርግ በምግብም ሆነ በመጠጥ በኩል የተፈጸመ  የማደንዘዝ ወንጀል ሊሆን እንደሚችል በሚከተሉት ሁለት ነጥቦች ልናሳይ እንወዳለን።

1 /አብራሪዎች ከበረራ በፊት በቂ እረፍት ስለሚኖራቸው በመዳከም ሊሆን አይችልም

2/ የበረራው ጊዜ ከሁለት ሰዓት ተኩል አይበልጥም

3/ ሁለቱንም አብራሪዎች በአንድ ጊዜ የእንቅልፍ ድባብ አይጫናቸውም

የችግሩን ምንጭ  ለማወቅ በቅድሚያ በአብራሪዎቹ ላይ የደምና የሽንት ምርመራ ቢካሄድ በቀላሉ መልስ ይገኛል የሚለው ከሕክምና ባለሙያነት ጋር ያልተያያዘ፣ካለን ዝቅተኛ ግንዛቤ በመነሳትያለን አስተያዬት ነው።ያንንም የአዬር መንገዱ የሕክምና ባለሙያዎች እንዳደረጉ ተስፋ አለን።

ከተመሳሳይ አደጋ ይሰውረን!

ደግመን ደጋግመን እንደምናሳስበው ከሁለገብ ቀውስ ለመውጣትና አገራችንን እንደ አገር ለማስቀጠል በዬፊናው መጮህና ማውገዝ ብቻ ሳይሆን  በህብረት ተደራጅቶ መታገልና ሥርዓቱን መደምሰስ ነው።

የሕዝባዊ አንድነት ግንባር ይመስረት!የጎሰኞች ስርዓት ይወገድ!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!